የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 12
ADDIS ABABA 7th Day of February, 2020.

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፭/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል የተፈረመው የተፈጥሮ ጋዝ ማስተላለፊያ በይነ መንግስታዊ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ……….….ገጽ ፲፪ሺ፺፯

## Content

Proclamation No. 1175/2019

Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Djibouti on the Transit of Natural Gas Pipeline Ratification Proclamation ……..Page 12097

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፭/፪ሺ፲፪

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል የተፈረመው የተፈጥሮ ጋዝ ማስተላለፊያ በይነ መንግስታዊ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተፈጥሮ ጋዝ ማስተላለፊያ በይነ መንግስታዊ ስምምነት የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሳስ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባደረገው መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1175/2019

### AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENTS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE REPUBLIC OF DJIBOUTI ON THE TRANSIT OF NATURAL GAS PIPELINE RATIFICATION PROCLAMATION

**WHEREAS,** the Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Djibouti on the Transit of Natural Gas Pipeline has been signed on 15th February 2019 in Addis Ababa;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Facility Agreement at its session held on 24th Day of December 2019;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ‹‹በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል የተፈረመው የተፈጥሮ ጋዝ ማስተላለፊያ በይነ መንግስታዊ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፭/፪ሺ፲፪›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስታት መካከል የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የጋዝ ማስተላለፊያ ቧንቧ የበይነ መንግስታዊ ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫.አስፈጻሚ አካላት**

ይህን ስምምነት እንዲያስፈጽም የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Djibouti on the Transit of Natural Gas Pipeline Ratification Proclamation No.1175/2019''

2. **Ratification of the Agreement**

The Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Djibouti on the Transit of Natural Gas Pipeline signed on 15th February 2019 in Addis Ababa is ratified.

3. **Implementing Organs**

The Ministry of Mine and Petroleum is hereby designated to implement this Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On the 7th Day of February, 2020.**

**SHALEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**